በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 202581

ቀን፡- 26/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኘ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ረሂማ አብዱላሂ

ተጠሪዎች ፡-1.ከዲር ዮሱፍ በከር

2. ሰይዳ ረመዳን

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋራ የሆነ የእርሻ መሬት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ነዉ የተባለዉ ዉል ቀሪ እንዲደረግና ይዞታዉን ለማስለቀቅ እንዲሁም አላባ ለማስከፈል የቀረበ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠሪዎችና በስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ሙስጠፋ ዩሱፍ ላይ በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ለ30 ዓመታት በትዳር ተሳስረን አብረን ስንኖር በሐረር ክልል በድሬ ጠያራ ወረዳ በአቦከር ሙጢ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ዉስጥ ያለንን አንድ ጥማድ ከግማሽ የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰዉን የእርሻ መሬት ያለእኔ ፈቃድ በሕገ-ወጥ መንገድ ለአሁን ተጠሪዎች በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በአመት 20 ኩንታል ማሽላ በማምረት ማግኘት የምንችለዉን በኩንታል በብር 1200.00 ሂሳብ ብር 24,000.00 አሳጥዉኛል፡፡እየተቃወምኩ በመሬቱ ላይ ተጠሪዎች ቤት ሰርተዉበታል፡፡ስለሆነም

ዉሉ ሕገ-ወጥ ስለሆነ እንዲፈርስና የገነቡትን ቤት አፍርሰዉ ይዞታዬን እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ከአመልካች ጋር በጋራ የያዙት መሬት እንደሆነና ያለአመልካች ፈቃድ በማንኛዉም ሁኔታ ማስተላለፍ እንደሌለብኝ ባለማወቅ ለተጠሪዎች በማስተላለፌ ተጠሪዎች በእርሻ መሬታችን ላይ ቤት ሊሰሩበት ስለቻሉ በአመልካች ጥያቄ መሰረት ቢወሰን አልቃወምም የሚል ይዘት ያለዉ መልስ ሰጥተዋል፡፡2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ መኖሪያ ቤት ለመግዛት እየፈለጉ ባሉበት የስር 1ኛ ተከሳሽ በመሬቱ የመጠቀም መብታቸዉን ለማስተላለፍ ፈልገዉ የመጠቀም መብታቸዉን ብር 100,100.00 ሸጠዉልናል፡፡ የመሬት ባለቤትነት ለመዉሰድ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡መሬቱ በዚህ አግባብ እንደተላለፈልንና ቤት ስንሰራም አመልካች እያወቁ አልተቃወሙንም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 17912 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶና መርምሮ በቀን 26/01/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የስር 1ኛ ተከሳሽ ያለተጠሪ ፈቃድ ባልና ሚስት ሆነዉ ከአመልካች ጋር በጋራ ባለይዞታ የሆኑበትን የመሬት ይዞታ ለተጠሪዎች በሽያጭ በማስተላለፍ ያደረጉት ዉል የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68ን የሚቃረን በመሆኑ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 69 መሰረት ዉሉ ፈርሶ ተጠሪዎች የገነቡትን ግንባታ በራሳቸዉ ወጪ አፍርሰዉ መሬቱን ለቀዉ እንዲወጡና ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 04953 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 22/10/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ክስ የመሰረቱት ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን አለዉ በማለት ቢሆንም ግራ ቀኝ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች በመሆናቸዉ፣ዉሉ የተደረገበት የመሬት ይዞታ የሚገኘዉ በሐረሪ ክልል ዉስጥ የሚገኝ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርግ ምክንያት በሌለበት እንደፌዴራል ጉዳይ ተቀብሎ መዳኘቱ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካች ክስ ሲመሰርቱ በግምት ብር 24,000.00 ምርት የሚገኝበት መሬት እንደሆነ ጠቅሰዉ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ልክ የሚገመት ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ ለመዳኘት የሚያስችል ስልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በመ/ቁጥር 00124 ላይ በቀን 24/03/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አቤቱታቸዉን ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 07/10/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ግራ ቀኝ በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ መሆናችን ስለተረጋገጠ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ በመቁጠር ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ ሳለ ተጠሪዎችም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን እንደሌለዉ ገልጸዉ ያቀረቡት መቃወሚያ ሳይኖር ዉሳኔዉ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2 ስር የተደነገገዉንና በሰ/በ/ቁጥር 144613 ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት

የተፈጸመበት ነዉ፡፡እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብኩትን የሰበር አቤቱታ ምርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ አዞ ግራ ቀኝ የጽሁፍ ክርክር አቅርበን ለዉሳኔ በተቀጠረበት ቀን ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም በማለት ዉሳኔ የሰጠበት አግባብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 እና ከቁጥር 339-348 ስር ስለዉሳኔ አሰጣጥ የተደነገገዉን ሥነ ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማጣራት ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ወደኋላ ተመልሶ አያስቀርብም በማለት ዉሳኔ የሰጠበት አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 05/11/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ግራ ቀኝ በአንድ ክልል ዉስጥ ነዋሪ ስለሆንና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬትም በሐረሪ ክልል የሐረሪ ከተማ አካል ሆኖ የሚገኝ በመሆኑ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ያለዉ የከተማ ነክ ፍርድ ቤት በመሆኑ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፌዴራል ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ መዳኘቱ ስህተት ነዉ ተብሎ በመሻሩ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ በተጨማሪ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ ቆጥሮ በዉክልና ሥልጣን አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ አይደለም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔዉ በመሻሩ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካችና ተጠሪዎች ነዋሪነታቸዉ በአንድ ክልል ዉስጥ እንደሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡የክሱ ስረ ነገር እና በአመልካች የተጠየቀዉ ዳኝነት አመልካች ያለፈቃደ የጋራ ባለይዞታ የሆንኩበትን የእርሻ መሬት ባለቤቴ ለተጠሪዎች በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገዉ ዉል ቀሪ ሆኖ ተጠሪዎች እየተቃወምኩ የሰራሁትን ቤት አፍርሰዉ መሬቱን እንዲለቁ ይወሰንልኝ የሚል እንደሆነ ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡እንዲሁም ለክሱ መሰረት የሆነዉ ዉልም የተደረገዉም ሆነ ተሸጠ የተባለዉ መሬት የሚገኘዉ በሐረሪ ክልል ዉስጥ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘንድ ክሱ ሲቀርብ በሥራ ላይ በነበረዉ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2 መሰረት መደበኛ ነዋሪነታቸዉ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንደሆነ በተደነገገዉ መሰረት የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ መሆኑ ከተረጋገጠና ክርክር ያስነሳዉ ንብረት ግምት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ መሆኑ ካረጋገጠ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/4 መሰረት በዉክልና ጉዳዩን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ሆኖም በተያዘዉ ጉዳይ የግራ ቀኙ መደበኛ አድራሻ በአንድ ክልል ዉስጥ መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል የተደረገዉና እንዲፈጸም የታቀደዉ መሬቱ

በሚገኝበት ሐረሪ ክልል ዉስጥ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርግ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ በመቁጠር በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት መሻሩና ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በሰጠዉ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረረቡትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪዎችን ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የክልሉ ሰበር የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙን ከቀረበዉ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ እስካሁን የሰበር ችሎት ክርክሮችን የሚመራበት የተለየ ሥነ ሥርዓት ሕግ ባለመኖሩ በሥነ ሥርዓት ሕጎች ለመደበኛ ክስና ለይግባኝ ክርክሮች አመራር የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ለሰበር በሚሆን መልኩ አመሳስሎ ተግባራዊ የማድረግ የዳበረ የሰበር ችሎቶች አሰራር መኖሩ ግልጽ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ የክልልም ሆነ የፌዴራል የሰበር ሰሚ ችሎቶች የሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ሲጠቀሙ በሥነ ሥርዓት ሕጎች የተዘረጋዉን የክርክር ሂደቶች አፈጻጸም ቅደም ተከተል በተቻለ መጠን በጥንቃቄ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ለፍትሐ ብሔር ይግባኝ ክርክር አመራር በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 እና 338/1 መሰረት የይግባኝ ማመልከቻዉንና የመጀመሪያዉ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ የሰጠበትን መዝገብ ግልባጭ በመመርምርና ይግባኝ ባይን በመስማት መልስ ሰጭ ቀርቦ እንዲከራከር ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሰጠ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ሕግን መርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341፣343/1 እና 348/1 መሰረት ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል እንጂ ወደኋላ ተመልሶ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የይግባኝ ማመልከቻዉ በመሰረዝ መወሰን የሚችልበት ሥነ ሥርዓት አግባብ የለም፡፡በተመሳሳይ ለይግባኝ ክርክር አመራር የተቀመጠዉን ሥነ ሥርዓት በመጠቀም የሰበር ክርክር ሲመራም የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የሆነ ወገን መልስ አቅርቦ እንዲከራከር ከተደረገ በኋላ በስር ፍርድ ቤት የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩ ተመርምሮ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ከተባለ እንዲታረም ካልሆነም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ከሚወሰን በስተቀር ሂደቱን ወደኋላ በመመለስ የፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ተጠቅሶ በሰበር ችሎት እንዲመረመር የሚያስችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ የሰበር አቤቱታዉ የሚሰረዝበት አግባብ የለም፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዉ ከተከራከሩ በኋላ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመሰረዝ ትእዛዝ የሰጠበት መንገድ ሊታረም የሚገባዉ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡ሆኖም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት የይግባኝ ማመልከቻም ሆነ የሰበር አቤቱታን በመሰረዝ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር ሲታይ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ የማጽናት ያክል ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ

ነዉ፡፡በመሆኑም ከመነሻዉም ክርክሩ የፌዴራል ጉዳይ ባልሆነበት እንደፌዴራል ጉዳይ ተቆጥሮ የተወሰነበት የክርክር አመራር ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑና ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ስለሆነ እንደአዲስ ክስ ቀርቦበት ሥልጣን ባለዉ በሐረሪ ክልል ፍርድ ቤት ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ከመሆኑ አንጻር በማየት ከዚህ አኳያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዘንድ የተፈጠረዉን የክርክር አመራር ጉድለት አልፈነዋል፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17912 ላይ በቀን 26/01/2012 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04953 ላይ በቀን 22/10/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በመሻር የወሰነዉና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁጥር 00124 ላይ በቀን 24/03/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

2. ይህ ዉሳኔ አመልካች ሥልጣን ባለዉ የክልሉ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ አያግዳቸዉም፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ